የሰ/መ/ቁ. 43331

ሐምሌ 19 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ገመቹ ቡቻላ - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቶ በቀለ ኩማ(ቡቻላ) - በሌሉበት

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የውርስ ንብረት ክፍፍል የሚመለከት ነው፡፡ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ መዝገብ 22866 የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በማጽናቱ በውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል ሲል አመልካች አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር የተያዘው ጭብጥ በተጠሪ በኩል ክስ የቀረበለት የወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለማየት ሥልጣን የለኝም ያለውን የከፍተኛው ፍ/ቤት አጽንቶታል፡፡ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ጉዳዩ የውርስ ክርክር ነውና የወረዳው ፍ/ቤት ሥልጣን አለው ካለ በኋላ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ግራ ቀኙ ወደ ወረዳው ፍ/ቤት ሳይመልስ መወሰኑ እና ቀደም ሲል በክልሉ ሰበር ችሎት  የተወሰነ ነው ሲል የጠቀሰው መዝገብ ውሳኔ ይዘት አግባብነት ለመመርመር ሲባል ተጠሪ እንዲቀርብ ታዟል፡፡ ተጠሪ መጥሪያ ተቀብሎ መልስ አልሰጠም በዚሁ መልስ የመስጠት መብቱ ታልፏል፡፡

እኛም የቀረበውን አቤቱታ ከሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ አንፃር ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ እና ከአመልካች አቤቱታ መረዳት የተቻለው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው ክርክር የውርስ ንብረት የሚመለከት ነው፡፡ ቀደም ሲል አመልካች የአባቴን የውርስ ንብረት ድርሻ ያካፍለኝ ሲል ተጠሪ ያቀረበው ክስ በቀበሌው በማህበራዊ ፍ/ቤት ታይቶ ከተወሰነለት በኋላ አመልካች እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርቦ የክልሉ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 4665 በሰጠው ትእዛዝ የአሁን አመልካች (ሥር ተከሳሽ) የመከላከያ ምስክር ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱን በመንቀፍ ይህው እንዲፈፀም ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱን፣ከዚያም ክርክር ተደርጐ ከተወሰነ በኋላ በይግባኝ በድጋሚ ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲደርስ ተጠሪው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የውርስ ንብረት መጠየቁ ተገቢ አይደለም ተብሎ መሻሩን ተጠቅሷል፡፡ እንግዲህ ለአሁኑ የሰበር ማመልከቻ መነሻ የሆነው ክርክር ከዚህ በኋላ በአደሳ መልክ የተጀመረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ካገኘ በኋላ የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ለወረዳው ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ወረዳው ፍ/ቤት የክልሉን የገጠር መሬት አዋጅ ቁጥር 110/99 በመጥቀስ የይዞታ ክርክር በቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት መታየት አለበት ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ከፍተኛው ፍ/ቤቱም ይህንኑ አጽንቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይህንን ውሳኔ ለመስጠት የጠቀሰው ምክንያት በግራ ቀኙ መካከል ያለው ክርክር የውርስ ንብረት የሚመለከት በመሆኑ የወረዳው ፍ/ቤት ሥልጣን አለው የሚል ነው፡፡ እንግዲህ የጉዳዩ አመጣጥ ይህንን የመሰለ መሆኑን ከተረዳን የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ፍሬ ነገሩ ላይ ውሳኔ መስጠቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 341/1/ በግልጽ እንደተመለከተው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሥር በመጀመሪያ መቃወሚያ ብቻ የወሰነውን ውሳኔ የለወጠ እንደሆነ የሥር ፍ/ቤት ወደ ክርክሩ ገብቶ እንደገና እንዲመለከተው መዝገቡን ሊመልስለት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ በርግጥ የዚህ ድንጋጌ የተቀመጠው መሪ ቃል አስገዳጅ ሆኖ አይታይም፡፡ ነገር ግን በግራ ቀኙ በኩል የሚቀርቡት የፍሬ ነገር ክርክሮች እና ማስረጃዎች በአግባቡ ለማጣራት ይቻል ዘንድ ለሥር ፍ/ቤት

መመለሱ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ በተለይም በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን የፍሬ ነገር እና የማስረጃ ክርክር ከመመርመር እና ማጣራት አንፃር የመጨረሻው የሥልጣን እርከን በመሆኑ የግራ ቀኙን የይግባኝ እድል የሚያጣብብ መሆኑንም መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ የመ/ደረጃው ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ስልጣን የለኝም ሲል መዝገቡን መዝጋቱ እንጂ አመልካች ያነሳው የይርጋ ክርክርም እልባት ያልተሰጠው ነጥብ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት በተገቢው ሥነ-ሥርአት ክርክር ያልተደረገበትን ፍሬ ነገር ጉዳይ በዚያው አጠቃሎ ውሳኔ መስጠቱ የሙግት አመራር እና የሥነ-ሥርአቱን የሥልጣን ክፍፍል መነሻ ሐሳቦች በአግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ከሥነ-ሥርአት መርህ አንፃር ስሕተት ያለው ሆኖ አግኝተናል፡፡

ከዚህም ሌላ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ በይዘቱም ሲታይ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የንብረት ክፍፍል ጥያቄ ማቅረቡ ተገቢ አልነበረም ሲል ከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ ጉዳዩ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሶ በአዲስ መልክ ተጠሪ የወራሽነት ማስረጃ ይዞ ክስ አቅርቦ በሥልጣን ጉዳይ ውሳኔ ተሰጥቶበት ከፍተኛው ፍ/ቤት ያፀናውን ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሁለት የከፍተኛ ፍ/ቤት መዛግብት በማጣመር የሰጠው ውሳኔም ሥነ-ሥርአቱን ተከትሎ የቀረበ አይደለም፡፡ በመጨረሻም ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የጠቀሰው የሰበር መ/ቁ. 4665 ንብረት ይከፋፈሉ የሚል ሳይሆን የአመልካች የመከላከያ ምስክር እንዲሰማ ወደ ሥር ፍ/ቤት የተመለሰ ከመሆኑ አንፃር ሲታይ የግራ ቀኙ የፍሬ ነገር ክርክር በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአግባቡ ያልተጣራ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ስለሆነም የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 22866 የሰጠው ውሳኔ ከሙግት አመራር መርህ እና ሥነ-ሥርአት አንፃር መሰረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡ የክልሉ ሰበር ችሎትም ይህንኑ ማረም ሲገባው ማለፉ ተገቢ አይደለም፡፡

ስለሆነም ውሳኔው ሊታረም ይገባል ብለናል፡፡ ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22866 በ26/03/2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 24680 በ27/4/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሻሽሎ ተከታዩ ተወስኗል፡፡
2. የግራ ቀኙ ክርክር የውርስ ጉዳይ ነውና የወረዳው ፍ/ቤት የመዳኘት ሥልጣን አለው ሲል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል፡፡
3. በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን የፍሬ ነገር ክርክር የወረዳው ፍ/ቤት መዝገቡን አንቀሳቅሶ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥበት ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341/1/ መሰረት መልሰናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ